**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**አንደኛ ሰበር ሰሚ ችሎት**

**ሰ/መ/ቁ 271003**
**ሰኔ 25 ቀን 2018 ዓ/ም**

ዳኞች፡- ቴዎድሮስ ምህረት

ብርሃኑ አመነዉ

ገበየሁ ፊለቀ

በዕዉቀት በላይ

ተሾመ ሽፈራዉ

ደጀኔ አያንሳ

ነክር ሱፋ

አመልካቾ/ች/ ፡- መ/ር አዲሱ ጸጋዬ

ተጠሪ/ዎች/ ፡- ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1. ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለዉ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተቋቋመባቸዉ ክልሎች የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ህገ መንግስታዊ የዉክልና ስልጣኑ መሠረት ያየዉን ጉዳይ የይግባኝ ክርክሩን ተመልክቶ ለመወሰን የይግባኝ ሰሚነት ስልጣን ያለዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ነዉ ወይስ የዚያዉ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነዉ ለሚለዉ የህግ ጥያቄ አግባብነት ያለዉ የህግ ትርጉም ለመስጠት ነዉ ፡፡
2. ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉም አመልካች የሲዳማ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁ 07468 መጋቢት 13 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 264921 ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በዚህ ችሎት

እንዲታረምላቸዉ መስከረም 01 ቀን 2017 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸዉ ምክንያት ነዉ ፡፡

3. ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለዉ አመልካች ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ተቋም ዉስጥ መምህር ስሆን ከተጠሪ ጋር ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም በተደረገ የአገልግሎት ስምምነት ዉል ለአራት ዓመት እስከ ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ ከስራ ግዴታ ዉጪ በመሆን የሶስተኛ ድግሪ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም ትምህርቴን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተምሬ ለስምንት ዓመት አገልግሎት ለመስጠት ፤ተጠሪ ደግሞ በየወሩ ደመወዝ እና የተለያዩ ክፍያዎችን ሊከፍለኝ የተስማማን እና ይህ ስምምነት በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርቱ የማያልቅ ከሆነ የሚሻሻልበትን አግባብ ለማመቻቸት የተስማማን በመሆኑ በዚህም መሰረት በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርቱን በግዜዉ መጨረስ ስላልቻልኩ ዉሉ እንዲራዘም ጠይቄ ተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 2014 ዓ/ም ለሁለት ዓመት ማለትም ከነሐሴ 03 ቀን 2014 ዓ/ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2016 ዓ/ም ዉሉን ያራዘመ በመሆኑ ነሐሴ 30 ቀን 2015 ዓ/ም የማራዘሚያ ዉል ፈጽመናል ፡፡ ይሁን እንጅ ተጠሪ በተሻሻለዉ ዉል መሰረት እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2015 ዓ/ም በየወሩ ደመወዝ ሲከፍለኝ ቆይቶ ከጥር 01ቀን 2015 ዓም ጀምሮ በዉላችን መሰረት ሊከፍለኝ ስላልቻለ ተጠሪ በዉሉ መሰረት ያልከፈለኝን የሰባት ወር ጠቅላላ ደመወዝ ብር 88053.00 /ሰማኒያ ስምንት ሽህ ሃምሳ ሶስት ብር / እና በየወሩ የቤት ኪራይ አበል ፤የትራንስፖርት አበል እና ለጽሑፍ መሳሪያ መግዣ እና ለኮፒ የሚከፈለኝ ክፍያ ከመጋቢት ወር 2014 ዓ/ም ጀምሮ የተቋረጠ ስለሆነ በጠቅላላ ብር 29750 /ሃያ ዘጠኝ ሽህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር/ ከወለድ ጋር እንዲከፈለኝ ፤ በዉላችን አንቀጽ 2(5) መሰረት ተጠሪ ዉል ያፈረሰ በመሆኑ ብር 30000 /ሰላሳ ሽህ ብር / ቅጣት እንዲከፍለኝ እንዲሁም አመልካች ወደ ተጠሪ ተቋም ተመልሼ አገልግሎት እየሰጠሁ ትምህርቴን እንድጨርስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የሚጠይቅ ነዉ ፡፡

4. ተጠሪ በሰጠዉ መልስ ከአመልካች ጋር በመጀመሪያ በፈጸምነዉ ዉል ከህዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም እስከ ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ለአራት ዓመት አመልካች በሚሉት አግባብ የተስማማን ሲሆን ይህንን ግዴታችንን ከተወጣን በኋላ አመልካች ትምህርቱን ባለመጨረሱ ለተጨማሪ ሁለት ዓመት እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2015 ዓ/ም ድረስ የዉል ግዜዉ የተራዘመ ሲሆን በዚህም

ግዜ ዉስጥ ግዴታችንን የተወጣን በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም አመልካች ዉሉ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2015 ዓ/ም የተራዘመ መሆኑን እያወቁ እና ይህም የተፈቀደበት ቃለ ጉባኤ እያለ ሆን ብለዉ በሀሰት የሌላ ቃለ ጉባኤ ቁጥር በመሙላት ዉሉ ተራዘመዉ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2017 ዓ/ም ነዉ የሚሉት ትክክል እንዳልሆነ እና መስተካከል እንዳለበት ተገልጾላቸዉ የተስተካከለዉ ላይ የፈረሙ በመሆኑ አሁን ያቀረበዉ ክስ ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል ፡፡

5. ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የሐዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ/ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2016 ዓ/ም የሚቆይ የማራዘሚያ ዉል ያደረጉ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የተጠሪ አካዳሚክ ኮሚሽን አመልካች እና ተጠሪ ያደረጉት ዉል ማራዘሚያ ሳይሻር እና በዉሉ ላይ የተመለከተዉ የዉሉ ቆይታ ጊዜ 2016 ዓ/ም ሳይደርስ አመልካች ሁለት ዙር ጭማሪ የትምህርት ፈቃድ ማራዘሚያ ጊዜ እስከ 6 ዓመት የጨረሱ ስለሆነ ለአንድ ዓመት ከክፍያ ጋር ተራዝሟል ፤ በማለት በቃለ ጉባኤ ያስቀመጠዉ የህግም ሆነ የዉል መሰረት የሌለዉ በመሆኑ ተጠሪ በገባዉ ዉል መሰረት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል እንዲሁም የተፈቀደዉ የትምህርት ማራዘሚያ ጊዜ በ2016 ዓ/ም ሲያልቅ አመልካች ወደ ስራቸዉ ተመልሰዉ ለአመልካች አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል ፡፡

6. ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች እና ተጠሪ የትምህርት ግዜ ማራዘሚያ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2015 ዓ/ም ያደረጉ መሆኑን የቀረበዉ ዉል የሚያስረዳ እና ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ዉሉ የተራዘመዉ እስከ 2016 ዓ/ም ነዉ በማለት ይከራከር እንጅ ያቀረበዉ ዉል ላይ የተጠሪ ተቋም ትምህርት ዓመት ሜይ 22 ቀን 2022 በተወያዩት ቃለ ጉባኤ ፈቅዶልኛል በሚለዉ ላይ በዚያዉ ቀን የተወያዩት ቃለ ጉባኤ እስከ 2016 ዓ/ም ብለዉ እንዳልተስማሙ ቃለ ጉባኤዉ የሚያረጋግጥ ሆኖ ሳለ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ለአመልካች እስከ 2016 ዓ/ም አራዝሟል በማለት ያልተከፈለ ደመወዝ እና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈለዉ እንዲሁም ወደ ስራዉ ይመለስ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የግራ ቀኙን ዉል

በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ሙሉ ለሙሉ በመሻር ዉሳኔ ሰጥቷል ፡፡

7. በዚህ ዉሳኔ ያልተስማሙት የአሁን አመልካች ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የይግባኝ ቅሬታዉን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዝ ሳይቀበላቸዉ ቀርቷል ፡፡
8. የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን አጭር ይዘቱም ተጠሪ የፌደራል ተቋም በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 እና ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 204107 በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ እንዲሻር ዳኝነት ጠይቀዉ በፍሬ ጉዳዩም ተፈጽሟል የሚሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ዘርዝረዉ አቅርበዋል ፡፡
9. የአመልካች የሰበር አቤቱታ እና የሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን የመራበትን ትዕዛዝ ተመርምሮ ክሱ የጀመረዉ በሐዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ይግባኙን ሊመለከት የሚገባዉ በሐዋሳ ከተማ ተደራጀዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍር ቤት ነዉ ወይስ የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚለዉን ከኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ፤የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ለማደራጀት ከወጣዉ አዋጅ ቁጥር 322/1995 አንቀጽ 2 እና ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20465 ከሰጠዉ የህግ ትርጉም አንጻር መርምሮ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ ተሰጥቷል ፡፡
10. ተጠሪ ቀርቦ በሰጠዉ መልስ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ለማደራጀት የወጣዉ አዋጅ ይዘት የሚያስረዳዉ በአምስት ክልሎች ማለትም በአፋር፤ ሱማሌ፤ጋምቤላ ፤በቤንሻንጉል፤ እና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች የሚገኙ ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ቀደም ሲል በፌደራል ጉዳይ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 በተሰጣቸዉ የዉክልና ስልጣን ስለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆነዉ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸዉ ጉዳዮችን ተቀብለዉ ለማየት እና ለማስተናገድ ተሰጥቷቸዉ የነበረዉ ስልጣን ቀሪ መሆኑን የሚያሳይ እንጅ የእነዚህ ክልሎች ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ባላቸዉ የዉክልና ስልጣን ያዩትን የፌደራል ጉዳይ በይግባኝ ተቀብለዉ ለማየት ያላቸዉን ስልጣን ያስቀረ አዋጅ አይደለም ፡፡ ክሱ የተጀመረዉ በአዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80

እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ለማደራጀት በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 322/1995 አንቀጽ 2 እና የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20465 ከሰጠዉ ትርጉም አንጻር የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወቅቱ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ስልጣን አለዉ ፡፡ በመሆኑም ከተጠቀሰዉ የህገ መንግስት አንቀጽ እና ከአዋጁ እንዲሁም የሰበር ዉሳኔ አንጻር የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለዉ ተብሎ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል ፡፡ በፍሬ ጉዳዩም ዝርዝር መልስ አቅርቧል ፡፡ አመልካችም የሰበር ቅሬታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል ፡፡ ሰበር ባለ አምስት ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ከፍርድ ቤቶቹ ስልጣን አንጻር የሚከተለዉን ጭብጥ ይዟል ፡፡

11. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 30 ቀ ን 1995 ዓ/ም ባደረገዉ ስብሰባ በአፋር ክልል ፤በቤንሻንጉል ክልል፤ በሶማሌ ክልል፤ በጋምቤላ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንዲደራጁ በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሰረት መወሰኑ ፤አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 78(2) በተሰጣቸዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን መሰረት በተጠቀሱት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ የፌደራል ጉዳዮች በተጀመሩበት ፍርድ ቤቶች ታይተዉ እንደሚወሰኑ ፤ ይህም ቢሆን ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ለማድረግ እንደሚችል ፤ እንዲሁም አዋጁ ከመጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ስለመሆኑ መደንገጉ በአዋጁ ተመልክቷል ፡፡

12. በሌላ በኩል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20465 ላይ በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሰረት የቤንሻንጉልን ጨምሮ የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በህገ መንግስቱ በተሰጣቸዉ የዉክልና ስልጣን መሰረት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ያዩዋቸዉን የፌደራል ጉዳዮች በይግባኝ ተቀብሎ የማየት ስልጣን ያላቸዉ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 322/95 እና በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(2) መሰረት ትርጉም ሰጥቷል ፡፡

13. ይህ የሰበር ትርጉም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል

እንዲደራጅ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሊወሰን እንደሚችል ከሚደነግገዉ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(2) ፤ በዚህ መልኩ ምክር ቤቱ ወስኖ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በከፊል ከተደራጀ የተደራጀዉ ፍርድ ቤት የሚኖረዉ ስልጣን ቀጥታ ክስ እና የይግባኝ ስልጣን መሆን አለመሆኑን የቀጥታ ክስም ሆነ የይግባኝ ስልጣን ይኖራቸዋል ከተባለ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የሰበር ትርጉም የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ባላቸዉ የዉክልና ስልጣን ያዩዋቸዉ የፌደራል ጉዳዮች በይግባኝ ተቀብለዉ የማየት ስልጣን ያላቸዉ ስለመሆኑ የተሰጠዉ ትርጉም ተገቢ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ የተያዘዉን ጉዳይ መወሰን ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ከአምስት በላይ ዳኞች በተሰየሙት ሊታይ ይገባል በሚል በአዋጅ ቁጥር 1234/2014 አንቀጽ 26 (1) መሰረት በአምስት ዳኞች ብይን ተሰጥቶ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚደንት በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 26(2) መሰረት ጉዳዩ በሰባት ዳኞች ታይቶ እልባት እንዲያገኝ በመምራታቸዉ የቀረበ ነዉ፡፡በዚሁ መሰረት ጉዳዩን እንደሚከተለዉ መርምረናል ፡፡

14. በዚህ መዝገብ እንዲወሰን የቀረበው ጭብጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውክልና የተነሳባቸው ክልሎች የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወክሎ ያያቸውን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣን የየትኛው ፍርድ ቤት ነው የሚለው በተመለከተ የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20465 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ጸንቶ መቀጠል ወይም መቀየር ያለበት መሆኑ ነው፡፡ ሕገ መንግስታዊው ውክልናው ስልጣን ጸንቶ ባለበት ጊዜ ጉዳዩ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚታይ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ጥያቄ የሚሆነው ውክልና በተነሳባቸው ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለተደራጀ አሻሚ ሁኔታ በመኖሩ ጥያቄው ሊነሳ ችሎዋል፡፡ ጸንቶ ባለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ጉዳዩ መታየት ያለበት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው የሚል አቋም ተይዞ የቆየ ሲሆን ከላይ እንደቀረበው ይህ ውሳኔ መለወጥ አለበት በሚል ምክንያት ጉዳዩ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ችሎት እንዲታይ ቀርቧል፡፡ ስለሆነም ምላሽ የሚያሻው ነጥብ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደራጀባቸው ክልሎች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ስልጣን በመጠቀም በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርብ ይግባኝ የማየት ስልጣን

የክልል ፍርድ ቤቶች ነው የሚለው አስገዳጅ ውሳኔ መለወጥ ያለበት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡

15. በዚህ መዝገብ የተነሳው ጉዳይ የፍርድ ቤቶች የስልጣን እርከን በተለይም በፌዴራል ሥርዓት ውስጥ በክልልና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚኖረውን የስልጣን ክፍፍል የሚመለከት በመሆኑ የዚህን ጽንሰ ሐሳባዊ ዳራ እና ሕገ መንግስታዊ ማዕቀፍ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በፌዴራል ሥርዓት መለያ ከሆኑት መሰረታዊያን ባህሪያት አንዱ በክልልና በፌዴራል መንግስቱ መካከል የሚደረገው የሥልጣን ክፍፍል ነው፡፡ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ላይ ስናተኩር የስልጣን ክፍፍሉ ከሶስቱ መንገዶች አንዱን ሊከተል ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ትይዩ ስርዓት (Dualist Model) ሲሆን በዚህ አወቃቀር ውስጥ ራሳቸውን ችለው ተለይቶ በተሰጣቸው የስልጣን ክልል በተናጠልና ራሳቸውን ችለው የሚሰሩ የፍርድ ቤት እርከኖች ይኖራሉ፡፡ ሁለተኛው የተቀናጀ ሥርዓት (Integrated Model) ሲሆን በዚህ አካሄድ ክልልና ፌዴራሉ መንግስት በመተባበር የሚሰሩ ከመሆኑም በላይ የስልጣን ንብብር የሚታይበትም ስርዓት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ የተማከለ ስርዓት (Centralized) ሲሆን ይህም በመላ አገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ የዳኝነት አካል እንዲኖር የሚያስችል ነው፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት የዳኝነት ስልጣን ክፍፍሉ ትይዩ የዳኝነት አካላት እንደሚኖሩ ከግምት ገብቶ የተፈጸመ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የፌዴራልና የክልል ዳኝነት አካላት በአጠቃላይ የየራሳቸው ተለክቶ የተሰጣቸው የዳኝነት ወሰን አላቸው፡፡ የዚህ ድልድልን አተገባበር ስናይ ግን የስልጣንን ክፍፍሉ ዘይቤው (ሞዴል) አሻሚነት የሌለው ቢሆንም በክልል የፌዴራል የመጀመሪያ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ባልተቋቋመባቸው ክልሎች የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን በውክልና እንዲያዩ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ይህ አተገባበር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ ሊቀየር መቻሉ ሲታይ የውክልና መፍትሔው መሰረታዊ የስልጣን ክፍፍል አምዱን ወይም ሞዴሉን ጠብቆ ያለ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ስለሆነም በመሰረታዊነት ሕገ መንግስቱ የዳኝነት ስልጣኑን ያደላደለበት ጽንሰ ሐሳባዊ ንድፍ ትይዮ ፍርድ ቤቶችን የሚከስት ሲሆን ይዘቱም የሚያሳየው እያንዳንዱ የዳኝነት አካል ተፈጥሮአዊ ስልጣኑ በሕገ መንግስቱ ተሰፍሮ የተሰጠው ብቻ መሆኑን ነው፡፡

16. ከዚህ የአወቃር ስልት በመነሳት በኢፌዲሪ ሕግ መንግስት የበየነውን የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ስናይ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ጉዳይ ላይ፤ የክልል ፍርድ ቤቶች በክልል ጉዳይ ላይ የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ሕገ መንግስቱ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የክልል እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን ሰፍሮና ለክቶ አከፋፍሏል፡፡ ፍርድ ቤቶች በመሰረታዊነት ስልጣናቸው የሚመዘዘው ከዚህ ክፍፍል ወይም ድልድል ሲሆን አንድ የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤት ስልጣን አለኝ ብሎ ጉዳይ ለማየት የሚችለው እና በመሰረታዊነት ስልጣኑ ሊሆን የሚችለው ከዚህ ድንጋጌ በሚቀዳ ተሰፍሮ ከተሰጠው ስልጣን ገደብ ውስጥ የሆነ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና እንዲያዩ የተሰጣቸውን ስልጣን ተግባራዊነት ጋር በተያያዘ ከሕግ መንግስቱ የሥልጣን ክፍፍል አንጻር መታየት አለበት፡፡

17. በሕገመንግስቱ አንቀጽ 78(2)፣ (4) እና 80(2) በተመለከተው መሰረት የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን ለማየት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ስልጣን ተፈጥሮአዊ ወይም ሕገ መንግስቱ ስልጣን ካከፋፈለበት ቀመር የሚቀዳ ሳይሆን በጊዜያዊነት ለክልሎች የተሰጠ ነው፡፡ ለዚህም በቂ ማሳያ ተደርጎ ሊጠቀስ የሚችለው የውክልና ጽንሰ ሐሳብን ተክትሎ የስልጣኑ ባለቤት የሆነው የፌዴራሉ መንግስት ሲወስን ይህን ስልጣን መልሶ መውሰድ መቻሉ ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 78(2) መሰረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአገሪቱ በሙሉም ሆነ በከፊል እንዲደረጁ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሊወስን ይችላል፡፡ በዚህ አግባብ በአዋጅ ቁጥር 322/1995 ምክር ቤቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን በከፊል የአገሪቱ ክፍል ለማደራጀት ወስኗል፡፡ በግልና በሕዝባዊ ግንኙነቶችም ሆነ እነዚህን በሚገዙ ሕጎች መሰረታዊ የሆነው መርህ የውክልና ስልጣን የስልጣኑ ሕጋዊ ባለቤት ወይም ተሾካሚ በሆነው በወካዩ ያለገደብ ተመልሶ ሊወሰድ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው የምክር ቤቱ ውሳኔም የዳኝነት ስልጣኑ ባለቤት የሆነው የፌዴራል መንግስት ውሳኔ ስልጣኑን ወደተፈጥሮአዊ ባለቤቱ የመለሰ ነው፡፡ በተቃራኒው በግልጽ እስካልተመለከተ ድረስ የዚህ እርምጃ ውጤትም የሚደራጀው ፍርድ ቤት የሚኖረውን ስልጣን ሳይቀነስ እና ሳይገደብ ምልዑ

እንደሚሆን ወይም በጣማራነት ወይም በውክልና ተይዞ የቆየውን ስልጣን ሳይሸራረፍ ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚመልስ መሆኑ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡

18. ይህ አረዳድ እንዳለ ሆኖ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በዋናነት መታየት ያለበት ፍርድ ቤቱ የተደራጀው እንደ ፍርድ ቤት በመሆኑ የተሰጠው ስልጣን ከፊል ነው ብሎ መደምምደም የሚያስችል የሕግ መነሻ ስለመኖሩ ነው፡፡ በአጠቃላይ ፍርድ ቤቱ ሲደራጅ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በዚህ ደረጃ እንዲያዩ የተሰጠው ስልጣን ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስልጣኑ ከሕግ መንግስቱና ከሕግ የሚመነጭ በመሆኑ ክልከላው ከግልጽ ድንጋጌ እስካልመነጨ ድረስ ለክርክር ወይም ለውይይት የሚቀርብ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ አንድ ፍርድ ቤት የሚቋቋመው ሙሉ የዳኝነት ስልጣን እንዲደኖረው ተደርጎ ሲሆን ስለገደብ መኖር እና የገደቡ ትክክል መሆን አለመሆን መነጋጋር የሚቻለው ይህን ውጤት የሚያስከትል ግልጽ ድንጋጌ ካለ ብቻ ነው፡፡

19. ከላይ በቀረበው ሕገ መንግስታዊ ማዕቀፍ ውስጥ የታወጀው አዋጅ ቁጥር 322/1995 የተጠቀሱት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የውክልና ስልጣን እንዲያበቃ ውሳኔ የተላለፈበት ነው፡፡ የአዋጁ ይዘትም ቢታይ የሚደራጀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ስልጣን በቀጥታ ንባብም ሆነ በአንድምታ፣ በግልጽ ይዘትም ሆነ በትርጉም ለመገደብ ወይም ለመቀንበብ መታሰቡን የሚጠቁም ይዘት የለውም፡፡ በመሰረቱ አዋጁ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በተጠቀሱት ክልሎች እንዲደራጁ ከማድረግ ባለፈ ስልጣንን የሚወስን ወይም የሚያከፋፍል አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ተደራጀ ማለት የሚኖረው ስልጣን ከሕገ መንግስቱና ከፍርድ ቤቶች ሚቋቋሚያ አዋጅ የሚመነጭ በመሆኑ ይህንን ነጥብ የሚመለከት ድንጋጌ ማካተቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ስለሆነም ምክር ቤቱ ፍርድ ቤቶቹ እንዲደራጁ ሲወስን ይህንንም በሕግ ሲደነግግ እነዚህ ፍርድ ቤቶች በሚሰሩበት የግዛት ክልል ውስጥ ሙሉ ስልጣን እንደሚኖራቸው ቀጥሎ የሚመጣ ተፈጥሮአዊ ውጤት ነው፡፡ ስልጣን ከሕግ የሚመነጭ በመሆኑ የተደራጁት ፍርድ ቤቶችም ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ ያለው ስልጣን ያለምንም ገደብ እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው፡፡

20. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን አሻሚ እንዳልሆነ ተጨማሪ ማሳያ የሚሆነው በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ሕጉ ያስቀመጠውን መፍትሔ ስናይ ነው፡፡ እንኳን

ወደፊት የሚከፈቱ መዝገቦች ይቅርና በተጠቀሱት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ዘንድ በመታየት ላይ ያሉትም ጉዳዮች ቢሆኑ ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዛውረው ሊታዩ የሚችሉበት አማራጭ በአዋጁ ተካቷል፡፡ አዋጁ በቀጣይ ስለሚከፈቱ መዝገቦች ጉዳይ ያላነሳው ከላይ እንደተጠቀሰው ምላሽ የሚሰጠው በሌላ ሕግ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ግልጽ ስለሆነም ጭምር ነው፡፡ በክልል ፍርድ ቤቶች በሂደት ላይ ያሉትን ጉዳዩች በተመለከተ ግን የአዋጁ አንቀጽ 3 ጉዳዮቹ በተጀመሩበት ፍርድ ቤት እልባት እንደሚያገኙ አስቀምጦ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን በተቃራኒው መወሰን እንዲችል ስልጣን ሰጥቷል፡፡ ከዚህ መረዳት የምንችለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተደራጀ በኂላ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ወደፊት የሚከፈቱትን የይግባኝ መዝገቦችን ብቻ ሳይሆን በመታየት ላይ ባሉትም መዝገቦች ስልጣን ስለማይኖራቸው ጉዳዮቹ በተጀመሩበት የሚወሰኑበት ወይም ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዛውረውም መታየት የሚችሉበት መንገድ ሕጉ አመቻችቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ ወደፊት ስለሚቀርቡ የይግባኝ ጉዳዮች ምንም ብዥታ እንደሌለው ተጨማሪ በቂ ማሳያ ተድርጎ ይወሰዳል፡፡

21. ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ፍርድ ቤቶችን በተወሰኑ ክልሎች ለማደራጀት በተዘጋጀዉ ረቂቅ አዋጅ ላይ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕግ እና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ መጋቢት 05 ቀን 1995 ዓ/ም በተደረገዉ የዉይይት ቃለ ጉባኤ ላይ ጉዳዩ ተነስቶ ይግባኝን በተመለከተ በክልሎች የሚቋቋሙት ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ብቻ እንጅ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ስለማይሆኑ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን የሚታዩ ቀጥታ ክስ ወንጀሎችን የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በዉክልና ማየት እንደሚቀጥሉ በዉክልና ያዩት ጉዳይ ይግባኝ የሚያስጠይቅ ከሆነ በክልሎች አዲስ የሚቋቋሙት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ይግባኙን እንደሚያዩ በግልጽ ባይቀመጥም ፍርድ ቤቶች ያለዉን መደበኛ አሰራር ተከትለዉ የሚሰሩ በመሆናቸዉ ችግሩ እንደማይፈጠር እና በዚሁ መሰረት በክልሎች የሚቋቋሙት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶችን የዉክልና ስልጣን ወስደዉ እንደሚሰሩና እነሱ ያዩዋቸዉ ጉዳዮችም ይግባኝ ሲቀርብባቸዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን የሚያይ ስለመሆኑ በአራቃቂው ቡድን ማብራሪያ ቀርቦ ይህንን

የሚቃረን ሌላ አስተያየት በቃለ ጉባኤዉ ላይ እንዳልሰፈረ ቃለ ጉባኤዉን አስቀርበን ተመለክተናል፡፡ ስለዚህ መነሻ ሰነዶችም ከዚህ በላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር በሚዛመድ መልኩ ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ የተሰጠ ከመሆኑም በላይ አጠቃላይ የሕጉ የመነሻ ሰነድ ይዘት ይህን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

22. ሕገ መንግስቱ የፌዴራል ጉዳዩች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንደሚዳኙ ነገር ግን በክልሎች የሚነሱ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ የፌዴራል ጉዳዮች በቅደም ተከተል በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚስተናገዱ ደንግጎ ይህ የሚቀጥለው ግን የሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ለማደራጀት እስከሚወስን መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አዋጅ ቁጥር 322/1995 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲያደራጅ ወዲያኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቱን ስልጣን ከራሱ ተፈጥሮአዊ ስልጣን ጋር በጣምራነት ይዞ በውክልና ሲተገብር የነበረው የክልል ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዩች ላይ ያለውን ስልጣን ያጣል፡፡ በዚህ መሰረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀጥታ ብቻ ሳይሆን በይግባኝ ያለው ስልጣን ቀሪ ሆኖ ወደተደራጀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መተላለፉ ሕገመንግስታዊና ሕጋዊ ነው፡፡

23. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ውሳኔ ላይ ወይም በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ ጉዳዩች ላይ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 13 ተመልክቷል፡፡ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን በተመለከተ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ስልጣን ተጠቅመው የሚሰሩ በመሆኑ ውሳኔያቸው እንደፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሚወሰድ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ እስከተደራጀ ድረስ ይግባኙ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍርድ ቤቱ ስልጣን በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ ጉዳዩችን ስለሚጨምር ስልጣኑ ዝግ ተደርጎ ወይም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 የተመለከተውን ብቻ አድርጎ መወሰድም አይቻልም፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 3(1)(ሐ) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ ወይም በፌዴራል መንግስት ሕግ በተገለጹ ቦታዎች ስልጣን እንደሚኖራቸው ተመልክቷል፡፡ የተደራጁት ፍርድ ቤቶችም በዚህ አግባብ ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግስቱ እና የአዋጅ ቁጥር 322/1995

በተጨማሪ በዚሁ አዋጅም የሚኖራቸው ስልጣን የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በወሰኑዋቸው የፌዴራል ጉዳችም ላይ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

24. የፍርድ ቤቶች ስልጣን ጉዳይ በሕገ መንግስቱ የተደረገውን የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ስራ ላይ ከማዋልና በሕግ ፊት ዋጋ ያለው የሚተገበር ውሳኔ ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነው። በአንድ ጉዳይ ላይ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን ውሳኔው ዋጋ እንዳያጣ ከማድረግም በላይ ፍርድ ቤቱ ሊተወው የሚችለው ነገር አይደለም። አንድ ፍርድ ቤት አስገዳጅ ውሳኔ መስጠት እንዲችል በሚያየው ጉዳይ ላይ ስልጣን ሊኖረው ይገባል። የስልጣኑ ምንጭ ደግሞ ሕግ ነው። በተያዘው ጉዳይ የሚደራጀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚያየው ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ በሕግ መንግስቱ ተግባራዊ በተደረገው የስልጣን ክፍፍል ቀመር መሰረት የፌዴራል ጉዳይ ላይ ይግባኝ ተቀብሎ የማየት ስልጣን ይኖረዋል። ይህ ከሆነ ውክልና በተነሳበት ሁኔታ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳችን በተመለከተ ስልጣን አላቸው በሚል የሚቀርበውን ክርክር የሕግ መሰረት መፈተሽ ያስልጋል።

25.ክልሎች በየፍርድ ቤቶቻቸዉ ማቋቋሚያ አዋጆቻቸዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር ያለዉን እና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዉክልና በሚያያቸዉ የፌደራል ጉዳዮች ላይ በሚቀርብ ይግባኝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማየት ስልጣን እንዳለዉ መደንገጋቸዉን ከየፍርድ ቤቶች መቋቋሚያ አዋጆቻቸዉ መረዳት የሚቻል ነዉ ። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያክልም የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 7 (3) ድንጋጌ ስር በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር ያለዉን እና የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዉክልና በሚያያቸዉ ጉዳዮች ላይ በሚቀርብ ይግባኝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማየት ስልጣን እንዳለዉ ተመልክቷል ። ይሁንና ይህ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤት የሆነዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባልተቋቋመባቸዉ ክልሎች እንጅ እንዳሁኑ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንዲያይ በተቋቋመበት ሁኔታ ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም በዋነኝነት የክልል ፍርድ ቤቶች ተፈጥራዊ ስልጣናቸዉ የክልል ጉዳዮችን ለማየት እንጅ የፌደራል ጉዳዮችን ለማየት አይደለም (የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(3) ድንጋጌን ይመለከቷል) ። የፌደራል

ጉዳዮችን የሚያዩት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(2) እና 80(2/4) እና (5) ድንጋጌዎች መሰረት በተሰጣቸዉ የዉክልና ሥልጣን መነሻነት ነዉ ። ይኸዉም የሚሰራዉ የፌደራል ፍርድ ቤት ባልተቋቋማባቸዉ ክልሎች የፌደራል ፍርድ ቤትን የስራ ጫና ለመቀነስ ወይም ክፍተት ለመሙላት ታስቦ እንጅ የፌደራል ፍርድ ቤት በተቋቋመበት ሁኔታ በተደራቢነት እንዲሰሩ ነዉ ተብሎ ሊወሰድ አይችልም ።

26. አሁን እየታየ ያለው የፌዴራል ጉዳዩችን በተመለከተ ስለሆነ የፌዴራል ጉዳዩችን የመዳኘት ዳኝነታዊ ስልጣንም ሆነ እርከኑ የሚኖረው ድልድል የሚወሰነው ሕገ መንግስቱ እና የፌዴራል ሕግ ነው። በዚህ መሰረት ተፈጥሮአዊ የሆነው የክፍፍል ቀመር የፌዴራል እና ክልል ጉዳዮች የሚለው ሲሆን በክልል የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አለመደራጀታቸው ታሳቢ ተደርጎ ክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ስልጣንም በጣምራነት እንዲኖራቸው ተደርጓል። ክልሎችም ይህን መሰረት አድርገው በሕጎቻቸው ውክልና ስልጣንን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ይዘት ማካተት ይችላሉ። ይህ ግን ጸንቶ የሚቆየው የሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት በክልል በሚታዩ ፌደራል ጉዳዮች ላይ በተለየ ሁኔታ ውሳኔ እስከሚያሳልፍ ድረስ ብቻ ነው።

27. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በእነዚህ ክልሎች የማቋቋሙ አስፈላጊነት በክልሉ ዉስጥ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በዉክልና የሚታዩ ጉዳዮችን ለማስቀረት እና በራሱ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ ለማድረግ መሆኑ ግለጽ ነዉ። አከራካሪዉ ጉዳይ በክልሎቹ የሚቋቋመዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚያያቸዉ ጉዳዮች ቀጥታ ክሶችን ብቻ ነዉ ወይስ ይግባኝንም ይጨምራል የሚለዉ ጉዳይ ላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20465 ፤54577 እና በሰ/መ/ቁ 204107 ላይ በሰጣቸዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች በክልል የሚቋቋሙት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚያዩዋቸዉ ጉዳዮች ቀጥተኛ ክሶችን ብቻ እንጅ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣኑ የሚያያቸዉን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣንን እንደማይጨምር አስገዳጅ ዉሳኔ ሰጥቷል ። ለዉሳኔዎቹ መሰረት የተደረጉት ምክንያቶችም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2) መሰረት የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ህገ መንግስታዊ የዉክልና ስልጣኑ ያያቸዉን የፌደራል ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣኑ በህገ

መንግስቱ አንቀጽ 80(5) ድንጋጌ ስር በግልጽ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ስልጣን ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደራጀዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2) መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርቡትን ቀጥተኛ የፌደራል ጉዳይ ክርክሮች ተቀብለዉ እንዲያስተናግዱ ተሰጥቷቸዉ የነበረዉን ስልጣን የተሰጠዉ እንጅ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንገስቱ አንቀጽ 80(5) መሰረት በይግባኝ ያላቸዉን ስልጣን ሁሉ የሚያስቀር አይደለም የሚል ነዉ፡፡

28.በመሰረቱ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ባላቸዉ ሕገ መንግስታዊ ዉክልና በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣናቸዉ ስር የሚያዩዋቸዉ ጉዳዮች የፌደራል ጉዳይ እስከሆኑ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 13 (1) ስር ደግሞ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀጥታ ያየዉን ጉዳይ በይግባኝ የማየት ስልጣን አለዉ ተብሎ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ያየዉን ጉዳይ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ እስከተቋቋመ ድረስ ስልጣኑ በቀጥታ የሚቀርቡ የፌደራል ጉዳዮችን ለማየት ብቻ ነዉ ለማለት የሚቻል አይደለም ፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ በተሰጣቸዉ የዉክልና ስለጣን በይግባኝ ሊያዩ እንደሚችሉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(5) ድንጋጌ ስር የተመለከተዉ በክልል ደረጃ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባልተቋቋመባቸዉ ያሉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶችን እንጅ የጉዳዩ ባለቤት የሆነዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተቋቋመባቸዉ ክልሎች ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም ፡፡ ምክንያቱም የፌደራል ጉዳይን ለማየት ተብሎ የተቋቋመዉ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እያለ ጉዳዩን በይግባኝ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይየዉ ማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን መቋቋም በከፊል ዋጋ እንደማሳጣት የሚቆጠር ነዉ ፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሎች ከተቋቋመ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ በቀጥታ የሚቀርቡ ክሶችን ብቻ ተቀብሎ እንዲያይ ነዉ ብሎ መዉሰድም ምክንያታዊ ነዉ ለማለት የሚቻል አይደለም ፡፡

29. ይህ የሚያሳየዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተቋቋመባቸዉ ክልሎች ያሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በፌደራል ህገ መንግስት በተሰጣቸዉ ዉክልና መሰረት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣናቸዉ በቀጥታ ያዩዋቸዉን ጉዳዮች በይግባኝ ማየት ያለባቸዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ባላቸዉ ህገ መንግስታዊ ዉክልና ሳይሆን በዚያዉ ክልል የተቋቋሙት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች መሆናቸዉን ነዉ ፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በአፋር፤ ሱማሌ፤ጋምቤላ ፤በቤንሻንጉል፤ እና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልሎች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታመኖበት በ2/3ኛ ድምጽ በአዋጅ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ የተደረገዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በእነዚህ ክልሎች በሙሉ ሥልጣኑ ማለትም በቀጥታም ሆነ በይግባኝ ሊያቸዉ የሚገባዉን የፌደራል ጉዳይ እንዲያይ ለማደረግ እንጅ ቀጥተኛ ጉዳዮችን ብቻ እንዲያይ ነዉ ብሎ መደምደም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(2) ድንጋጌ መሰረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 322/95 ዓላማ የሚያሳካ ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም ፡፡

30. ሲጠቃለል ከላይ በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች መሰረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተቋቋመባቸዉ ከላይ በተመለከቱት አምስት ክልሎች ያሉ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(4) ድንጋጌ በተሰጣቸዉ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዉክልና ስልጣን በቀጥታ ያዩዋቸዉን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣን ያላቸዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሳይሆኑ በክልሉ ዉስጥ እንዲቋቋሙ የተደረጉት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ናቸዉ ተብሎ ተከታዩ ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ ተሰጥቷል ፡፡

## ዉሳኔ

1. ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁ 20465 ፤54577 እና በሰ/መ/ቁ 204107 ላይ የተሰጡ ትርጉሞች ተለዉጠዋል ፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 322/1995 መሰረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደራጀባቸው ክልሎች ያሉ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78(2) እና 80(4) ድንጋጌ በተሰጣቸዉ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዉክልና ስልጣናቸዉ በቀጥታ ያዩዋቸዉን

የፌዴራል ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣን ያላቸዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሳይሆኑ በክልሉ እንዲደራጁ የተደረጉት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ናቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ አምስት ዳኞች ለተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት ተመልሷል ፡፡

## የልዩነት ሃሳብ

እኛ በ5ኛ፣ በ6ኛ እና በ7ኛ ላይ የተሰየመነዉ ዳኞች ቀደም ሲል የተሰጠዉ የህግ ትርጉም ሊለወጥ ይገባል በሚለዉ በአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ ስለማንስማማ የልዩነት ሃሳባችንን እንደሚከተለዉ አስፍረናል፡፡

የህግ አፈፃፀምና አተረጓጎም ወጥነትና ተገማችነት በአንድ አገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወት ዉስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠዉ እሴት ነዉ፡፡ በህግ ስርዓት ዉስጥ ወጥ ትርጉምና ተገማችነት እንዲኖር በማድረግ ረገድ የሰበር ስርዓት ዓይነተኛ ሚና እንዳለዉ ይታወቃል፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3) ላይ እንደተመለከተዉ፣ በአገራችን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በሰበር የማረም ስልጣን ለፌዴራል እንዲሁም ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ሲሆን፣ ዓላማዉን አስመልክቶ በሕገ-መንግስቱ እንዲሁም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ በግልጽ የተመለከተ ድንጋጌ ባይኖርም፤ በሀገሪቱ ዉስጥ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎም ሥርዓት ማስፈን፣ ትክክለኛ የሕግ አተገባበር ሥርዓት እንዲኖር እንዲሁም የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ የማድረግ ዓላማ ያነገበ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ሲጸድቅ ከፍርድ ቤቶች ስልጣን ጋር በተያያዘ ከተያዘዉ ቃለ ጉባኤ፣ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 መግቢያ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸዉ ዉሳኔዎች እንዲሁም በዙሪያ ከተፃፉ ድርሳናት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሰበር ችሎቱ ይህን ኃላፊነቱን ሲወጣ የሚሰጣቸዉ ዉሳኔዎች (የህግ ትርጉሞች) የሚናበቡ እና አንዱ ከሌላዉ ጋር የማይጋጭ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ይጠበቃል፡፡ ችሎቱ ህግን በመተርጎም የሚሰጠዉ ዉሳኔ በየትኛዉም ደረጃ በሚገኝ ፍርድ ቤት አስገዳጅነት እንዳለዉ በመደንገግ በአገራችን ታሪክ

የመጀመሪያዉ የሆነዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 454/97 አንዱ ዓላማዉ ተደርጎ የቀረበዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች ለአንድ የህግ ድንጋጌ የሚሰጡት የተለያየ ትርጓሜ የህጉን መንፈስና ዓላማ እንዳያዛባ እንዲሁም አተረጓጎሙ ተገማች እንዲሆን ስለመሆኑ ህጉ በህዝብ ተወካይ ምክር ቤት ሲጸድቅ ከቀረበ ሀተታ ዘምክንያት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየዉ ለሰበር ችሎቱ የተሰጠዉ ስልጣንና ኃላፊነት ከፍተኛ መሆኑን፣ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሚሰጣቸዉ የህግ ትርጉሞችም ወጥ እና ተገማችነት ያላቸዉ ሊሆኑ የሚገባ መሆኑን ነዉ፡፡

የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ባለዉ የበላይ ፍርድ ቤት የሚሰጥ ዉሳኔ በተለይም በአንድ ጉዳይ ከሚሰጥ የህግ ትርጉም ከተገማችነት አኳያ አሉታዊ ጎን ሊኖረዉ የሚችል ቢሆንም፣ ግዙፍ የሆነ የህግ ስህተት ያላቸዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች ጸንተዉ ሊቀጥሉ አይገባም፡፡ በመሆኑም በዳኝነት ሥርዓቱ ዉስጥ ወጥነትንና ተገማችነትን የማስፈን መሠረታዊ ዓላማ እንዲሁም ማህበረሰቡ በዳኝነት አካሉ ላይ ሊያሳድረዉ የሚችለዉን እምነት ከፍ ማድረግን ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ግዙፍ የሆነ ስህተት የተፈጸመበት ዉሳኔ ዉሳኔዉን በሰጠዉ በእራሱ ፍርድ ቤት በጥንቃቄ የሚከለሱበትን ሥርዓት ማበጀት ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ይመስላል፣ አዋጅ ቁጥር 454/97 በአንቀጽ 1/2/ ላይ ለዚሁ ዕዉቅና ይሰጣል፡፡ ይሁንና ችሎቱ በምን ምክንያትና እንዴት ቀደም ሲል የሰጠዉን የህግ ትርጉም እንደሚለዉጥ በግልጽ እና በዝርዝር ያስቀመጠዉ መስፈርት የለም፡፡ ችሎቱ አንድ ጊዜ የያዘዉ አቋም በዘፈቀደ ወይም ያለ በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ቶሎ ቶሎ የሚለወጥ ከሆነ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ወጥነትና ተገማችነት ጥያቄ ዉስጥ ይገባል፤ ብሎም ማህበረሰቡ በችሎቱ ላይ ያለዉን እምነት ሊሸረሽር ይችላል፡፡ የበላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ዉሳኔ ለተወሰነ ጊዜ ረግቶ መቆየት እንዳለበት፣ የዉሳኔዉ/የትርጉም ቶሎ ቶሎ መቀያየር የህግ ስርዓቱን ሊጎዳ እንደሚችል እንዲሁም በህግ ፊት እኩል የመቆጠር መብትንም ጥያቄ ዉስጥ ሊያስገባ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን በማስታወስ አንድ ጊዜ የተሰጠ ዉሳኔ/የህግ ትርጉም ያለ በቂ እና አሳማኝ ምክንያት መቀያየር እንደማይገባ በዙሪያዉ የፃፉ የህግ ባለሙያዎች ይመክራሉ፡፡ ይህንን ከግምት ዉስጥ በማስገባትም የበላይ ፍርድ ቤቶች አስቀድመዉ የሰጡትን የህግ ትርጉም/ዉሳኔ የሚለወጥበትን ሁኔታ ጥብቅ መስፈርቶችን ያስቀምጣሉ፡፡ በሲቪል ሎዉ ህግ ተከታይ አገሮች፣ በተለይ በፈረንሳይ፣ የሰበር ሰሚ ችሎት አሰራር ቀደም ብሎ የተሰጠ የህግ ትርጉም በራሱ በሰበሩ ፍርድ ቤትም ቢሆን ሊለወጥ የሚችልበት ጥብቅ ስርዓት

ተዘርግቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በኮመን ሎዉ ህግ ተከታይ አገሮችም ከዚህ በፊት የተሰጠንና በህግ መልክ በማገልገል ላይ ያለን ዉሳኔ ለመቀየር አሳማኝ እና አስገዳጅ ምክንያት መኖሩን ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26(1) ሰበር ሰሚዉ ችሎት በአንድ ጉዳይ ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ የያዘዉን አቋም መለወጥ የሚችለዉ በዘፈቀደ ሳይሆን በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች ሲቀርቡ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 14(2) በሁለት ምክንያቶች ሰበሩ አስቀድሞ የያዘዉን አቋም ሊለዉጥ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የመጀመሪያዉ አንድ የሰበር ዉሳኔ ከሌላ የሰበር ዉሳኔ ጋር ሲጋጭ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ በተለያዩ ምክንያቶች መለወጡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ነዉ፡፡ በሁለት የሰበር አቋሞች መካከል ተቃርኖ ሲኖር ከሁለቱ ዉሳኔዎች/የህግ ትርጉሞች የተሻለዉን ተፈፃሚ በማድረግ ተቃርኖዉን ማስታረቅ በመሆኑ ያን ያህል አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ አስቸጋሪ የሚሆንና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያሻዉ ተቃርኖ ሳይኖር አስቀድሞ የተያዘዉን አቋም የመለወጥ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህን ማድረግ አስቀድሞ የተሰጠዉን ዉሳኔ ሊያስቀይር የሚችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ስለመኖሩ ወይም የቀደመዉ ዉሳኔ/የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት መሆኑን እርግጠኛ መሆንን ይጠይቃል፡፡ የዉሳኔዉ ጸንቶ መቀጠል የሚያስከትለዉን ተጽዕኖ የዉሳኔዉ መለወጥ ከሚያስከትለዉ ተጽዕኖ አንፃር ማመዛዘንንም የግድ ይላል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በሰ/መ/ቁጥር 20465፣ 54577 እና 204107 ላይ ቀደም ሲል በሰጠዉ ዉሳኔ የያዘዉ አቋም እንዲለወጥ ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት መኖር አለመኖሩን ቀጥሎ የተመለከቱትን ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ፈትሸናል፡፡

1. በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተነሳዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን እንጂ የይግባኝ ስልጣን ጭምር ነዉ ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(2) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳዮች ላይ ካለዉ ስልጣን በተጨማሪ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝት ስልጣን እንደሚኖረዉ ሲደነግግ፣ በአንቀጽ 80(5) ላይ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ የሰጠዉን ዉሳኔ

በይግባኝ የማየት ስልጣን እንዳለዉ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ ሕገ መንግስቱ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ጋር በተያያዘ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ያላቸዉን የመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን እና የይግባኝ ስልጣን ለያይቶ ያስቀመጠ መሆኑን ነዉ፡፡ በሌላ በኩል የተወሰኑ ክልሎች (በአዋጁ የተጠቀሱ አምስቱ ክልሎች) ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ያነሳዉ አዋጅ ቁጥር 322/95 አንቀጽ 2፣ በተጠቃሾቹ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንደሚደራጅ የሚደነግግ ሲሆን፤ በዚህ ሁኔታ የሚደራጅ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚኖረዉ ስልጣን የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በዉክልና በማየት የሰጠዉን ዉሳኔ በይግባኝ የማየት ስልጣን ጭምር ስለመሆኑ በግልጽ አይደነግግም፡፡

የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳዮችን ለማየት ያላቸዉ ስልጣን ስለሚነሳበት ሁኔታ የሚደነግገዉ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78(2)፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ በሁለት-ሦስተኛ ድምጽ ሊወስን እንደሚችል ካስቀመጠ በኋላ፤ ጉዳዩ በዚህ አኳኋን ካልተወሰነ የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ለክልል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል በሚል ይደነግጋል፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት ሲጸድቅ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78(2) ይዘት ጋር በተያያዘ ዉይይት ሲደረግ በዚህ ሁኔታ ለክልሎች የተሰጠ ስልጣን ዉክልና አለመሆኑን በጉባኤዉ የህግ ጉዳዮች ሰብሳቢ በግልጽ አንስተዉታል፡፡ የሰብሳቢዉ ሃሳብም ቃል በቃል *"….በ2/3ኛ ድምጽ ሊቀበለዉ እንደሚገባ የሚገልጽ ሲሆን ከዚህ ዉጪ ከሆነ ግን ስልጣኑ የክልሎች መሆኑን የሚያመላክት እንጂ ማዕከሉ ለክልሎች በዉክልና እንደሰጣቸዉ አድርጎ ያላስቀመጠ መሆኑን…"* የሚል ነዉ፡፡ ከዚህ የሰብሳቢዉ (የባለሙያዉ) ሃሳብ እንዲሁም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78(2) "….የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ለክልል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል" በሚል ከተመለከተዉ ኃይለቃል መገንዘብ የሚቻለዉ በዚህ ሁኔታ ለክልሎች የተሰጠዉ የዳኝነት ስልጣን ተራ ዉክልና አለመሆኑን፣ ይልቁንም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት-ሦስተኛ ድምጽ እስካልተነሳ ድረስ፣ ከጉዳይ ባህሪ ወይም ከተከራካሪ ወገኖች ማንነት (አድራሻ ወይም ዜግነትን ለማለት እንደሆነ ልብ ይሏል) አንፃር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ቢሆንም፣

ክልሎች በሚያስተዳድሯቸዉ የስልጣን ወሰን ዉስጥ የተነሳን ጉዳዩ የመዳኘት ስልጣን እንዳላቸዉ የሚያመላክት መሆኑን ነዉ፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 188483፣ 181923፣ 213214፣ 207869 እና በሌሎችም ላይ የሰጣቸዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉሞችም ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡

በዚህ ምክንያት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ እስካልተነሳ ድረስ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን ማየት እንዲችሉ የሚፈቅድ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ተራ ዉክልና ሳይሆን የክልል መንግስታትን በሚያስተዳድሩት ክልል ውስጥ ካላቸው የውሳኔ ሰጭነት ስልጣን ጋር የሚያያዝ ነዉ የሚባል ከሆነ፣ የፌዴራል ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የተነሳባቸዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በክልሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅን ጉዳይ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ አይቶ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ የማየት ስልጣን እንደሌላቸዉ በግልጽ በአዋጁ ሊመለከት ይገባል፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ጉዳዮች ላይ ያላቸዉን የመጀመሪያ ደረጃ እና የይግባኝ ስልጣን ሕገ መንግስቱ ለያይቶ ያስቀመጠ ከመሆኑ አኳያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በተወሰኑት ክልሎች እንደሚደራጁ በአዋጁ መደንገጉ፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚደራጁባቸዉ ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2) የተሰጣቸዉን የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን እንዳይኖራቸዉ ከሚያደርግ በስተቀር በአንቀጽ 80(5) ላይ የተመለከተዉን የይግባኝ ስልጣንን ጭምር እንዲያጡ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

በአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ እንደተመለከተዉም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚደራጅባቸዉ ክልሎች ምክንያት የሚነሳዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(5) ላይ የተመለከተዉን የይግባኝ ስልጣን ጭምር የሚያጠቃልል መሆን አለመሆኑም አዋጁ (አዋጅ ቁጥር 322/95) ከመጽደቁ በፊት በህግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢነት በተካሄደ የአስረጂዎችና የባለሙያዎች መድረክ ላይ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበዉ ዉይይት የተደረገበት ስለመሆኑ ቃለ ጉባኤዉ ያሳያል፡፡ በዚህ ሁኔታ ለተነሱት ሃሳቦች ከአስረጂ ባለሙያዎች (አርቃቂዎች) አንዱ የሆኑት ባለሙያ ይግባኙ በክልሎች አዲስ የሚቋቋሙት ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንደሚታይ በግልጽ ባይቀመጥም ፍርድ ቤቶች ያለዉን መደበኛ አሰራር ተከትለዉ እንደሚሰሩ አስታዉሰዉ ችግር ይፈጠራል ብለዉ እንደማያስቡ

አስተያየታቸዉን የሰጡ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከአንድ ክልል በጽሑፍ በቀረበ አስተያየት ይህንኑ ያካተተ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን፣ በዚህ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ አለመስጠቱን፣ ይልቁንም የመድረኩ ሰብሳቢ የቀረቡ ጥያቄዎች መልስ እንደሚፈልጉ ጠቅሰዉ ፍትሕ ሚኒስቴርም ጥያቄዎቹን በጥልቀት ተመልክቶ አስተያየት እንዲሰጥባቸዉ በማሳሰብ የዕለቱ ስብሰባ መጠናቀቁን ከቃለ ጉባኤዉ ማየት ይቻላል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚደራጁባቸዉ ክልሎች ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣናቸዉ በማየት በሚሰጡት ዉሳኔ ላይ የሚቀርብን ይግባኝ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የማየት ስልጣን ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ በአዋጁ በግልጽ መመልከት ያለበት መሆኑ አለመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ዉይይት የተደረገበት ቢሆንም፣ ግልጽ ምላሽ በመድረኩ ያልተሰጠ መሆኑን ነዉ።

ከዚህ በኋላ አዋጁ ለኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ቀርቦ ሲጸድቅ ይህን ነጥብ አስመልክቶ በፓርላማ የተደረገ ዉይይት ምን እንደነበረ ሀተታ ዘ-ምክንያቱን ባለማግኘታችን ለማወቅ አልተቻለም። የሆነ ሆኖ ህግ አዉጪዉ የይግባኝ ስልጣኑን በግልጽ አላነሳም። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ብቻ የተገደበ ስለመሆኑ በወቅቱ ስራ ላይ በነበረዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 13 ላይ የተመለከተዉን ግልጽ ድንጋጌም አላሻሻለም። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚደራጅባቸዉ ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ ይግባኝ ለማየት በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(5) ላይ የተሰጣቸዉ የይግባኝ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 322/95 በግልጽ ተነስቶ በክልሉ ለሚደራጁ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ያልተሰጠ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 13 ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን በተመላካች (impliedly) ተሻሽሏል ማለት አይቻልም።

ህግ አዉጪዉ በተጠቃሹ አዋጅ የይግባኝ ስልጣን ማንሳት ቢፈልግ ኖሮ በአዋጁ ላይ በግልጽ ባያሰፍር እንኳ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የቀረበዉን ይግባኝ ብቻ እንደሚያይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ያሻሽላል ተብሎ ይጠበቃል። አዋጅ ቁጥር 25/88ን የተካዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 13(2) *"በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ ጉዳዮች"* የሚል ተጨማሪ ድንጋጌ የያዘ ቢሆንም፣ የፌዴራል ጉዳዮችን

የማየት ስልጣን የተነሳባቸዉ ክልሎች ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን በማየት በሚሰጡት ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚታይ በሌላ ህግ በግልጽ የተመለከተ ባለመሆኑ ከተያዘዉ ጉዳይ አኳያ ይህም አዋጅ ከቀደመዉ አዋጅ የተለየ ድንጋጌ የለዉም፡፡ በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ የተመለከተዉ እና በአዋጁ አንቀጽ 3(1)(ሐ) ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ ወይም በፌዴራል መንግስት ሕግ በተገለጹ ቦታዎች ስልጣን እንደሚኖራቸው የተመለከተዉም፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ ከተነሳበት ቦታ ጋር በተያያዘ የሚኖራቸዉን ስልጣን ለማመላከት (ለምሳሌ ድሬ ዳዋ ወይም አዲስ አበባ) ሲባል የተቀመጠ ድንጋጌ ከመሆኑ አኳያ ከይግባኝ ስልጣን ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀጽ 13 ላይ ለተመለከተዉ ድንጋጌ እንደ ማሟያ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚታዩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መወሰን እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 3(2) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም፣ አዋጁ ከመዉጣቱ በፊት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመታየት ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት ሁኔታ እንደሚታዩ ለሚደነግገዉ አንቀጽ 3(1) ልዩ ሁኔታ ነዉ ከሚባል በስተቀር አዋጁ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን ጭምር ስለ ማንሳቱ እንደ አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ የዳኝነት ስልጣን ምንጩ ህግ እንደመሆኑ መጠን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን በማየት በሚሰጡት ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ ተቀብሎ ማየት እንዲችል በግልጽ ስልጣን ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

በሕገ መንግስቱ በተዘረጋው የፌዴራል ሥርዓት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ካላቸው የጣምራነት ሥልጣን ባለፈ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78/2 እና 80(4-6) የፌዴራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንዲመለከቱ ሥልጣን ሰጥቷል፡፡ በዚህም ሕገ-መንግሥቱ የክልል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መታየት ያለባቸው የፌዴራል ጉዳዮች የዳኝነት ሥልጣን እንዲጋሩ(shared rule) በማድረግ የዳኝነት አገልግሎቱን ተደራሽነት ያረጋግጣል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ የዳኝነት አካል በፌዴራልና በክልል ደረጃ በየእርከኑ መዋቀሩ ሲታይ አደረጃጀቱ በተዋረድ ያለ የተይዩ አቀራረጽ (dual system) ያለው ቢሆንም የፌዴራልና የክልል ጉዳይን የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች መመልከታቸው የተደባለቀ (integrated system) እንደሚከተል አመላካች በመሆኑ ጉዳዩ የፌዴራል መሆኑ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል

ጉዳዮች ላይ ያለዉ የመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን መነሳቱ በይግባኝ የፌዴራል ጉዳዮችን የማየት ሥልጣኑ አንድ ላይ መነሳቱን አያመለክትም፡፡

በአጠቃላይ ከስልጣን እርከን አኳያ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን እና የይግባኝ ስልጣን በኢፌዲሪ ህገ መንግስት እንደቅደምተከተሉ በአንቀጽ 80(2) እና 80(5) ተለያይቶ መቀመጡ፣ በዚህም መነሻ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳዮችን በማየት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ በአዋጅ ቁጥር 322/95 በተጠቀሱት ክልሎች የሚደራጅ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑ በአዋጁ በግልጽ መደንገግ እንዳለበት በአስረጂዎችና የባለሙያዎች መድረክ ሃሳብ ቀርቦ እና ዉይይት ተደርጎ ነገር ግን በአዋጁ በግልጽ ሳይካተት መቅረቱ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ብቻ የሚገደብ መሆኑን የሚያሳይ የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 13 ድንጋጌ ሳይነካ ባለበት እንዲቀጥል መደረጉ እና ይህንኑ አዋጅ በተካዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ላይም በግልጽ የተመለከተ ድንጋጌ አለመኖሩ ሲታይ፤ ህግ አዉጪዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(5) መሠረት የተሰጣቸዉ የይግባኝ ስልጣን በግልጽ አለማንሳቱን ብቻ ሳይሆን ለማንሳት አለመፈለጉን የሚያሳይ ነዉ፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 20465 እና 54577 (በዚህ መዝገብ በአብላጫ ድምጽ የተለወጡት መዛግብት) ላይ ለሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት ያረገዉም የክልል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ጉዳዮች ላይ ያላቸዉ ስልጣን የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን እና የይግባኝ ስልጣን በሚል ለይቶ በህገ መንግስቱ የተመለከተ ቢሆንም፣ የይግባኝ ስልጣን በግልጽ አለመነሳቱን ነዉ፡፡ (በሰ/መ/ቁጥር 54577 ላይ ከተሰየሙት ዳኞች ዉስጥ አንዱ ዳኛ አስረጂ ሆነዉ ከፍ ሲል በተገለጸዉ የአስረጂዎችና የባለሙያዎች መድረክ ላይ በመገኘት በርካታ ሃሳቦችን ሲያነሱ የነበሩ መሆኑንም ልብ ይሏል)፡፡

2. የፌዴራል ጉዳዮችን በፌዴራል የመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣኑ በማየት በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ በግልጽ የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን (ዉጤት አልባ እንዲሆን) የሚያደርግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ዉሳኔ በዚህ ችሎት/በፍርድ ቤት ሊሰጥ አይገባም፡፡

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 7 (3) በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር ያለዉን እና የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዉክልና በሚያያቸዉ ጉዳዮች ላይ በሚቀርብ ይግባኝ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማየት ስልጣን እንዳለዉ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚደራጅባቸዉ ሌሎች ክልሎችም በፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጃቸዉ ተመሳሳይ ድንጋጌ አካተዋል፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ የተሻሻለዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 163/2011 አንቀጽ 6(2) እና የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 207/2014 አንቀጽ 26(2/ሐ) ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሲደነግጉ መነሻ ያደረጉት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(5) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የተነሳበት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳዮችን አይቶ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብን ይግባኝ የማየት ስልጣን እንዲኖረዉ በክልሉ ህግ አዉጪ አካል የተወሰነዉም በዚሁ መሠረት እንደሆነ እሙን ነዉ፡፡

የይግባኝ ሥርዓት በፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ባለዉ አካል በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ የፍሬ ነገር እና/ወይም የህግ ስህተትን በማረም በዉሳኔዉ ምክንያት መብቱ ተነክቷል የሚል ሰዉ (ይግባኝ ባይ) ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ የበታች ፍርድ ቤቶች ዳኞች መቆጣጠሪያ እና የተጠያቂነት ማረጋገጫ መንገድ ስለመሆኑ የሚታወቅ ነዉ፡፡ ስለሆነም የሲዳማ ክልልን ጨምሮ ከፌዴራል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን በአዋጁ የተነሳባቸዉ ሌሎች ክልሎች፣ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጣቸዉ ዉሳኔዎች ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን እንዳለዉ በግልጽ ሲደነግጉ፣ ህግ አዉጪዉ አካል እራሱ የሾማቸዉ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ እየተወጡ መሆን አለመሆኑን በይግባኝ ሥርዓት ለመቆጣጠር በማሰብ ጭምር ነዉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ፣ ምንም እንኳ ጉዳዩ ከመሠረቱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ቢሆንም፣ ከይግባኝ ስልጣን ጋር በተያያዘ ክልሎቹ የተለየ መብት/ጥቅም ይኖራቸዋል፡፡ ጉዳዩ

ከመሠረቱ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑ ክልሎች ከይግባኝ ጋር በተያያዘ ያላቸዉን መብት/ጥቅም እንዲያጡ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉ በአዋጁ በግልጽ የተነሳ እንደሆነ ነዉ፤ ከዚህ ዉጪ በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትርጉም ይህን ስልጣናቸዉን ሊያጡ አይገባም፡፡ ይሁንና ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ እንደተመለከተዉ የይግባኝ ስልጣኑ በግልጽ አልተነሳም፡፡ በአዋጁ በግልጽ ቢነሳ ኖሮ፣ የየክልሎቹ ህግ አዉጪ አካላት ከፍ ሲል በተመለከተዉ ሁኔታ በህጎቻቸዉ ያካተቱትን ድንጋጌ ያነሳሉ/ያሻሽላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የይግባኝ ስልጣኑ በአዋጁ (በአዋጅ ቁጥር 322/95) በግልጽ ባለመነሳቱም የፌዴራል ጉዳዮችን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣናቸዉ በማየት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን ዉሳኔ በይግባኝ ተቀብሎ የማየት ስልጣንን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለመስጠቱ የሚደነግገዉ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 7 (3) አሁንም እንደጸና ነዉ፡፡ ክልሉ ህግ አዉጪ አካል ይህን ድንጋጌ ጨምሮ አዋጁን ሲያወጣ፣ ክልሉ በእራሱ ጉዳይ እራሱ ለመወሰን ያለዉን ህገ መንግስታዊ መብት/ስልጣን በመጠቀም በመሆኑም በአዋጁ በዚህ ሁኔታ የተመለከተዉን ድንጋጌ ዉጤት አስመልክቶ የሚሰጥ ትርጉም ይህንኑ ከግምት ዉስጥ ሊያስገባ ይገባል፡፡ ከዉሳኔዉ መገንዘብ እንደሚቻለዉ፣ አብላጫዉ ድምጽ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 7(3) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የለዉም ሲል የሰጠዉ ምክንያት የድንጋጌዉ ተፈፃሚነት የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤት የሆነዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባልተቋቋመባቸዉ ክልሎች እንጅ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንዲያይ በተቋቋመበት ሁኔታ ሊሆን አይችልም በማለት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መታየት ያለበት ነጥብ፣ በክልሉ ደረጃ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደራጀቱ ወይም በአዋጁ እንዲደራጅ መወሰኑ ብቻዉን በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ በግልጽ የተመለከተዉ ድንጋጌ ዉጤት እንዳይኖረዉ ማድረግ አለማድረጉ ነዉ፡፡

ፌዴራልዝም እራስ በራስ የማስተዳደር (self rule) እና ከማዕከላዊ መንግስት ሥልጣንን የመጋራት(shared rule) ጽንሰ ሃሳብ ያጣመረ ነው፡፡ ስለፌዴራል መንግስት እና የክልል መንግስታት አወቃቀር የሚደነግገው የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50/1 የፌዴራሉም ሆነ የክልል መንግስታት ሕግ አውጪ፣ህግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት ሥልጣን እንደላቸው ይደነግጋል፡፡ ሁለቱም በሕገ-መንግስቱ ተለይቶ በተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ህግ የማዉጣት ስልጣን ያላቸው መሆኑን ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ

50(2)፣ 50(5) እና 55(1) ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻል ቢሆንም በፌዴራል እና በክልል ህጎች መካከል ግጭት ሲኖር ከሁለቱ የትኛዉ ተፈፃሚነት ሊኖረዉ እንደሚገባ ሕገ መንግስቱ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም በፌዴራል እና በክልል ሕጎች መካከል ግጭት በሚኖርበት ጊዜ ተፈፃሚነት ያለዉን ህግ የመምረጡ ሁኔታ የሕገ መንግስቱን የስልጣን ክፍፍል መርሆዎችን፣ በተለይም የፌዴራል መንግስትና ክልሎች የሕግ አዉጪነት፣ የሕግ አስፈፃሚነትና የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸዉ፤ የፌዴራሉ መንግስት ከፍተኛ የስልጣን አካል የፌዴራሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን፣የክልል ከፍተኛ የሥልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት መሆኑን፤ ለፌዴራሉ መንግስት የተሰጠዉ ስልጣን በክልሎች መከበር እንዳለበት፣ለክልሎች የተሰጠ ስልጣን በፌዴራሉ መንግስት መከበር እንዳለበት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50/8/፣ 50/2/፣50/3/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ ማስገባትን የግድ ይላል፡፡

በሌላም በኩል በፌዴራል ደረጃ በተዋቀረ ሰበር ሰሚ ችሎት በሚሰጥ የህግ ትርጉም የክልል ምክር ቤት ያወጣዉን ህግ መሻር ወይም ህጋዊ ዉጤት እንዳይኖረዉ ማድረግ፣ ከህግ ማዉጣት ስልጣን ጋር በተያያዘ በክልል ምክር ቤት ስልጣን ዉስጥ ጣልቃ እንደመግባት የሚቆጠር ሲሆን፣ ይህ መሆኑም በክልሎች ከፍተኛ የስልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት ስለመሆኑ እንዲሁም የፌዴራል እና የክልል መንግስታት አንዳቸዉ የሌላቸዉን ስልጣን ሊያከብሩ እንደሚገባ በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉን ድንጋጌ ይገዳደራል፡፡ በመሆኑም ከፌዴራል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በፌዴራል መንግስት በወጣዉ ህግ እና በክልል መንግስት በወጣዉ ህግ መካከል ግጭት ሲኖር ለጉዳዩ መፍትሔ ለመስጠት ተመራጭ የሚሆነዉ፣ የክልል ህግ አዉጪ አካል ተጠቃሹ ህግ ከፌዴራል ህግ ጋር በሚስማማ መልኩ እንዲያሻሽል ማድረግ ወይም ጉዳዩ የክርክር ጭብጥ ሆኖ ከቀረበ እና የግድ እልባት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ሆኖ ከተገኘም በፌዴሬሽን ምክር ቤት የህገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ማድረግ ነዉ፡፡

ከዚህ አኳያ ሲታይ፣ በተራ ቁጥር 1 በዝርዝር እንደተመለከተዉ፣ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣኑ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 322/95 በግልጽ ባለመነሳቱ ስለ ይግባኝ ስልጣን አስመልክቶ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 7 (3) ላይ ከተመለከተዉ ጋር የሚቃረን ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ የህጎች ግጭት አለ ለማለት የሚቻል አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣የህግ ግጭት አለ ቢባል

እንኳ መፍትሔ የሚሆነዉ ከፍ ሲል ከተመለከቱት የመፍትሔ አማራጮች አንዱ ስራ ላይ እንዲዉል ከማድረግ ዉጪ በዚህ ረገድ በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ የተመለከተዉን ግልጽ ድንጋጌ የመሻር ዉጤት የሚያስከትል የህግ ትርጉም ሊሰጥ አይገባም፡፡ በክልሉ ህግ አዉጪ አካል ያልተሻረ እና ጸንቶ ያለ የህግ ድንጋጌ ዉጤት አልባ እንዲሆን የሚያደርግ ትርጉም እንዲሰጥ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ በርግጥ በፌዴራል ህግ እና በክልል ህግ መካከል አለመጣጣም ሲኖር የፌዴራል ህግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚል አንድምታ ያለዉ የህግ ትርጉም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 209763 ላይ ተሰጥቷል፡፡ ከላይ በተመለከተዉ ምክንያት ይህን የልዩነት ሃሳብ ያሰፈርነዉ ዳኞች በዚህ የችሎቱ አቋም የማንስማማ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተጠቃሹ መዝገብ ላይ ለተሰጠ ዉሳኔ መነሻዉ የወንጀል ጉዳይ ሆኖ የወንጀል ኃላፊነት እና ቅጣትን ልዩ ባህሪ መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ ከዚህም አልፎ በመዝገቡ ላይ አከራካሪ የሆነዉን ጉዳይ አስመልክቶ የፌዴራል እና የክልል ህግጋት በግልጽ የሚጋጩ ስለመሆኑም ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በተጠቃሹ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ የህግ ትርጉም ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለዉም፡፡

በአጠቃላይ ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን ጋር በተያያዘ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 7(3) ላይ በግልጽ የተመለከተዉ ድንጋጌ ጸንቶ እያለ ይህን ወደ ጎን በመተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ተክቶ የፌዴራል ጉዳዮችን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣኑ በማየት በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይገባል ተብሎ ሊወሰን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

3. አተረጓጎሙ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚደራጁባቸዉ ክልሎች ነዋሪዎችን የፍትሕ ተደራሽነት ከግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡

አዋጁ (አዋጅ ቁጥር 322/95) በተወሰኑት ክልሎች እንደሚደራጁ የሚደነግግ ቢሆንም፣ በተጠቃሾቹ ክልሎች ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሟላ ሁኔታ አሁንም ድረስ እንዳልተደራጀ ይታወቃል፡፡ አዋጁ ሲነሳ የተጠቀሱት አምስት ክልሎች ቢሆንም፣ የቀድሞዉ ደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በተለያዩ ተጨማሪ ክልሎች መዋቀሩን ተከትሎ አሁን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቋቋሙባቸዉ ክልሎች ወደ ስምንት ከፍ ብሏል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ክልሎች ከፍተኛ ፍርድ ቤትን

ማደራጀት ተጨማሪ ወጪ እንዲሁም ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ ይህ መሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በመወከል የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚፈልግ ተከራካሪ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወዳለበት ለመሄድ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ለመጓዝ ይገደዳል፡፡ ከዚህም አልፎ ጉዳዩን ከክልሉ የስራ ቋንቋ ወደ ፌዴራል የስራ ቋንቋ መቀየርም የግድ ይላል፡፡ ይህ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖችን ለተጨማሪ ወጪ እና ድካም የሚዳርግ ነዉ፡፡ በድምር ዉጤቱም የፍትሕ ተደራሽነትን ጥያቄ ዉስጥ ያስገባል፡፡ በርግጥ ህጉ ግልጽ ከሆነ ተፈፃሚ እንዲሆን ከማድረግ በዘለለ የህጉን ይዘት ከእነዚህ ሁኔታዎች ማለትም ከአመቺነት ወይም ሌሎች ጉዳዩች አንጻር በማየት መወሰን አይቻልም፡፡ ነገር ግን እንደ ተያዘዉ ጉዳይ ዓይነት ያለ አከራካሪ ጉዳይ ሲኖር፣ በተለይም ጸንቶ ያለን አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔ ለመለወጥ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተገቢ የሚሆነዉ የሚሆነዉ ዜጎች ወይም ፍትሕ ፈላጊዎች ባነሰ ወጪና ድካም ጉዳያቸዉን ለፍርድ ቤት አቅርበዉ መብታቸዉን ማስከበር የሚችሉበትን አማራጭ መከተል ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር በተያዘዉ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተነሳዉ በርግጥም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ጭምር መሆን አለመሆኑ በዚህ ከዜጎች ፍትሕ ተደራሽነት አኳያ ልክ የተሻለ አማራጭ የሚሆነዉ የነበረዉ የህግ ትርጉም ሳይለወጥ ጸንቶ እንዲቀጥል ማድረግ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል በአዋጅ ቁጥር 322/95 በተወሰኑት ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንዲደራጁ መወሰኑን ተከትሎ በአዋጁ የተጠቀሱት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ጉዳዮች ላይ ያላቸዉን የይግባኝ ስልጣን በግልጽ አንስቷል ለማለት የሚቻል አለመሆኑ፣ በግልጽ አንስቷል ቢባል እንኳ በዚህ ረገድ ክርክሩ የተጀመረበት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ የፌዴራል ጉዳዮችን አስመልክቶ በክልሉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ በግልጽ የተመለከተዉን ድንጋጌ ዉጤት አልባ የሚያደርግ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊሰጥ የሚገባዉ አለመሆኑ፣ እንዲሁም አሁን ባለበት ሁኔታ በአዋጁ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቋቋሚባቸዉ ክልሎች ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በዉክልና በማየት በሚሰጡት ዉሳኔ ላይ ባነሰ ወጪ እና ድካም ይግባኝ አቅርቦ ለማሳረም ያላቸዉ መብት በተሻለ ሁኔታ የሚከበረዉ የነበረዉን ዉሳኔ በማስቀጠል በመሆኑ

ይህም በትርጉም ሂደት ከግምት ዉስጥ ሊገባ የሚገባ ከመሆኑ አኳያ በአጠቃላይ ሲታይ፤ የቀደሙትን የህግ ትርጉሞች ለማስለወጥ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ በዚህም ምክንያት ከባልደረቦቻችን በሃሳብ ተለይተናል፡፡